# የዛሬዎቹ ማሙሾች !!

## አበበ አረዳ

አይዞህ አትዘን አታልቅስ ! የዛሬው ማሙሽ !
የዛሬዋ ማሚትም አይዞሽ ! አትዘኝ አታልቅሽ !
ምንም እንባችሁን የሚያብስ ባይኖር !
ሥቃያችሁ በሥቃይ ላይ ቢደመር ፤
የትውልድ እርግማን ጋሳቢ .....
ባዶ ቤት ተረካቢ ...
የጥራጊ ሕይወት አራጋቢ
የምድርን ሰቆቃ አንጋቢ ...
እንዲያ በመሆናችሁ አዝናለሁ !
እኔም የትውልድ ባለዕዳ ነኝና እጅግ ተጸጽቻለሁ !
በጎ ምግባር ስላነሰኝ ይቅርታ እጠይቃለሁ !
እናት አባቶች ሁሉ እንደኔ ይቅርታ ጠይቁ :
ለትውልድ ያቆያችሁት ሰለሌለ በሃሰት አትመፃደቁ :

ጨዋነት ነው ይቅርታን መጠየቅ ፤ በዚህ ነገር አትፈሩ :
ለዚህ ትውልድ ግልጽ ሁኑለት በደላችሁን አትሰውሩ :
ጸሐይ ያንቃቃው ፤ ብርድ የጠበሰው ጉዳችሁ !
ብትሰውሩት አይሰወር ፤ አደባባይ ነው ገበናችሁ :
አታመልጡምና ከታሪከ-መዘክሩ !
ድክመታችሁን ዘክዝኩ ከስህተታችሁም ተማሩ !

ማሙሽና ማሚት በቀዳሚው ትውልድ እንዳትኮሩ :
ቀዳሚዎቹ አልገባቸው የክቡር ሥራ ምሥጢሩ :
አእምሯቸውን በጸበኛነት-ባኅሪ መርዘው :
ኅሣ-ብሔር-ብሔረ-ሰብ ፈልፍለው !
በጠባብ ስሜት ጸብ ጭረው.....
በሃይማኖት ባላንጣነት ተናንቀው.....
ሠርቶ በማደር ላይ ዶልተው ......
በብልጽግና ላይ አምጸው ፤ ድኅነትንም ታጥቀው !
ሥልጣኔን ጠልተው !
ድንቁርናን አጎልብተው !
ኋላ-ቀርነቱ ዙፋኑን ዘርግቷል ........
የዛሬዎቹ ማሙሾች : በርግጥ ጎልውናችሁ ተናግቷል !

እና ምን ይደረጋል ?
መቼም አንዴ ሆኗል !
አንዴ ሆኗልና ፤ እንደሆነስ ይቀራል ?
ወይስ በነገው ዓለማችሁ ነገር ሁሉ ይቀየራል ?
ያንንስ ማን ያውቃል ?
ግን የትውልድን ጥንካሬ ይጠይቃል :

ከቀዳሚው ትውልድ ደካማ ጎን መማሩ ፤
ከዚያ ላይ ነው የሚመስለኝ ምሥጢሩ !
ሠርቶ በማደር ያላመኑ ቀዳሚዎቹ ትውልዳችሁ ፡
ድኅነትና ተመጽዋችነትን ያስረከቧችሁ ፡
ነገር ቆርቋሪ ጸብ-ፈጣሪዎቹ ...
የክቡር ሥራ ቀባሪዎቹ ፡
ኅልውናን አናግተው ፡
የአንድነትን ፍቅር አጥፍተው ፡
የርስ-በርስ ጥላቻን አስፋፍተው !
የኋላ-ቀርነት መቅ ውስጥ ወርደው ፡
በዓለም ዝቃጭነት ተመዝግበው ፡
ውርሳችሁ ይኸው ሆነ ! የማሙሽና ማሚት ፡
የምድራዊው ሲኦል ድድቅ ጭለማ ቤት !
እግዚኦ አበስኩ ገበርኩ ! ጊዜው ምኑን ጉድ አሳያችሁ ?
በለጋ ወጣት ዕድሜያችሁ ፡
ከዕድገት ማነቆ ትውልድ ተፈጥራችሁ !
ጥራጊ ሕይወት ላይ ተጥላችሁ !
የምድርን ሰቆቃ ተቀላቢ በመሆናችሁ !
በቀዳሚ ትውልዳችሁ ላይ እንጂ ፤ በማንም እንዳታዝኑ ፡
በዕድልም አታማሩ ሌላውንም አትኮንኑ !

ቀዳሚ ትውልዶች ሠርቶ ለማደር ጊዜ አላገኙም ፡
ለጎሠኞነት አታካራ ግን ጨርሶ አልቦዘኑም ! ...
ሥንፍና እጅ እግራቸውን ቆልፎ ...
አእምሯቸው በጸብ ዛር ገዝፎ !
በሥልጣኔ ማደግን ንቀው !
በሥልጡኖችም ዘንድ ተገፍተውና ተዋርደው ፡
ፊተኞች ኋለኞች እንዲሉ ....ግን እኔ እንጃ !
ቀንቷቸው ይሆናል የኋሊቱ እርምጃ !
ለተከታይ ትውልዳቸው መከራን ሲደግሱ ፡
ሕዝብን በጎሣና-ዘር ሲያናክሱ !
አሁንም እዚያው ላይ ናቸው !
በሥራ ማደግ ምሥጢሩ ፍጹም ስላልገባቸው !..
ለዓለም ጭራነት ያበቃቸው !

ትናንት ከቅኝ ገዥዎች ቀንበር የተላቀቁ ፤
አንዳንዴም በመቆርቆር ፤ አንዳንዴም ሲሳለቁ ፡
እንዲህ ሲሉ ነበር ፤
የኛን ጉድ የኛን ነገር ....

"በጥንቱ ጊዜ ቅኝ-ገዢዎችን በትግላችሁ ስትበትኑ !
ለመላ አፍሪካ የነፃነት አርማ ስትሆኑ !
ኢትዮጵያ በኅብረት ትግሏ ጠንክራ ፤
አፍሪካን በሙሉ ተቆጣጥራ ፡
በአንድ በኩልም በእመቤትነቷ ኮርታ !
በሌላም በኩል ትሆንና የአፍሪካ አለኝታ
ሥጋት ፤ ፍርሃት ፤ ደስታችን ፡
ተደበላልቆ በውስጣችን ፡
እንዲያ ነበር ኢትዮጵያን የገመትናት ፡
እንደዛሬው ገበናዋ ሳይጋለጥባት !
ውስጠ-ምሥጢሯን ሳናውቅ የጎሠኞች ቅራኔ አብጦ !
ኅልውናዋን ገለባብጦ !
ለካስ የጎሠኞች ኢንስቲትዩሽን ነበራት ኢትዮጵያ !
የርስ-በርስ ጥላቻ መፍጠሪያ !
የሕዝብ ኅልውና መቅበሪያ !

የጥሩ ነገር አርአያ መስላችሁ !
የጥፋት ቀስት ምልክት በመሆናችሁ !
በጣም ነው ያፈርንባችሁ !!
ለዚያውም ከኛ ኋላ ቀራችሁ !
ዕውነትን የሚሻ መሪ አላፈራችሁ !
ኋላ-ቀርነቱ አልጸጸታችሁ !
ዝነኛ ምድራችሁ የዳቦ ቅርጫት የነበረች !
የቀን-ጅብ መሪዎችን አፍርታለች !
እነሱ በጦርነት ሕዝብን ሲያምሱ ፤
እናንተ ለፍትሕ ብላችሁ ሳትነሱ !
የጥንቱን ወኔ አጥፍታችሁ !
ጀንበር ስትጠልቅ በላያችሁ ፡
ዓለም በብዙ ስትርቃችሁ ፡
ደጋግማችሁ ወራሪዎችን እንዳላሸነፋችሁ ፤
እንዴት የቀን ጅቦች ይብሷችሁ ?

ምነው ጸጥ እልም ድርግም ጭልጥ አላችሁ ?
ዲክታተር መሪዎችን አቅፋችሁ !
የርስ-በርስ ፍጅቱ ጣማችሁ ?
የላችሁ ስንል አላችሁ !
አላችሁ ስንል የላችሁ ! "
ግራ ያጋባል ነገራችሁ ፤.......
እንደናንተም ባይብስ ! እኛምኮ አለብን ችግሩ ፤
የሃይማኖት ባላንጣነት የጎሣ አዶከበሬ ዛር ቅብጥርጥሩ !

የማንረሳው ነገር አለ ታዲያኮ !
የምኒልክ የዓድዋው ተጋድሎ ! ቅኝ-ገዥዎችን አንበርክኮ
ለአፍሪካ ሕዝብ የነፃነት ብርሃን ነበርኮ !
አርቲ-ቡርቲዎች ታሪከ-መዘክርን ላይሽሩ !
ያሻቸውን ቢቀባጥሩ !
የሃበሻን ወኔ ላይሰብሩ !
እስከዚህ ነበር ታላቅ ሕዝብ መሆናችሁን የምናውቀው !
የአፍሪካ ጭራ በመሆናችሁ ግን ! በእጅጉ ነው ያፈርነው ! "

ያሉንን ሰማችሁ ? ! የአፍሪካ ልጆች ሲያወጉ !
ነገሩ የቆረቆራችሁ ካላችሁም ! እስቲ መላ ፈላልጉ !
ብቻ........ ነገር ቢበዛ በአህያ አይጫንምና !
ብቻ... እህም...ብዙም ሲወራ ሆድ ባዶ ይቀራል ይባላልና !
ታሪኩ ባጭሩ ይኸን ይመስላል ማሙሾች !
የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች !
ኢትዮጵያኮ ታሳዝናለች !
ዲግሪም አፍራሽ ሆኖ ፤ አስተማሪ የለ ተማሪ ፡
ለብልጽግናም የቆመ የለ ሀገር ወገን አስከባሪ ፡
ብቻ ሁሉም የችግር ዘማሪ !
መዓት ቅስፈት አውሪ !
ለልማትና ዕድገት መሰናክል ፈጣሪ ፡
የጦር አዋጅ ነጋሪ !
በመፍትሔ አልቦ አእምሮ ፡ ነገር ወጣሪ አክራሪ ፡
የሽቀላ ፖለቲካ አነብናቢ ፡
ለግል ሥልጣን ተስገብጋቢ !
ታዲያ ከእንዲህ ዓይነቶቹ ቀዳሚ ትውልዶች ፡
ምን ይጠበቅ ነበር ማሙሾች ?
ተስፋችን በናንተ እንጂ እኛማ ግምት ውስጥ ገብተናል ፡
በታሪክ ሚዛን ተሠፍረን ቀለናል !
የመከራን ካባ ለትውልድ አልብሰናል !
መቼ እንደሚጠፋ የማይታወቅ የዘረኝነት እሳት አዳፍነናል ፡

ስማችን በዛሬው ትውልድ ፊት አድፏል !
አይለወጥ ነገር  አይሻሻል ፡
እጅግ ጎድፏል ! ቆሽሿል !
በመጪውም ትውልድ ፊት የባሰ ይጠላልና !  ያስረግማል !
እንግዲህ ማሙሽ !  ማሚትም በርቱ ንቁ !
ከኛ ምንም አትጠብቁ  !
እኛማ  ከአፍራሽ ሥራችን ጋር ወድቀናል !
ታሪከ-መዘክራችን አድፏል !
አይሻሻል !  አይታደስ  ! አያምርበት ምኑም...ምኑ ፡
የኛው ይቅር አይነሳ !  በራሳችሁ ተማመኑ !
መቼም ወላጆች ነንና ይቅርታችሁን አትንፈጉን ፡
የወላጅ ምርቃታችን ሁሌም ከናንተ ጋር ይሁን ፡
የኛን በደል ፈጽማችሁ እርሱ !
ግን ከደካማ ጎናችን ተነስታችሁ ራሳችሁን አድሱ !
ምናልባት በናንተ ብንጽናና !
ኢትዮጵያ ዳግም ገና !
የአንድነትን ጥቅም የሚያውቅ መሪ ተፈጥሮ ፡
ለዕድገት ሕዝብን አስተባብሮ ፡
ምድራችን ዳግም አረንጓዴ ለብሳ ብናያት !
ኢትዮጵያ ብትባል ዳግም የዳቦ ቅርጫት !
ማን ያውቃል ?
ይሆን ይሆናል !